የሰ/መ/ቁ 38601

ታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-**የኢትዩጵያ እህል ንግድ ድርጅት - ብርሃኑ አሻግሬ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ከድጃ ሳቢር ቀረበች ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው የአመልካች ሠራተኛ ለነበረው በሞት ለተለየው ባለቤትዋ ሊከፈል ይገባ ነበር ያለችውን ክፍያ እንዲከፈላት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የተጠሪ ባለቤት በሕይወት እያለ ክስ መስርቶ ከተከራከርን በኂላ በሕጉ መሠረት ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች ሁሉ ተከፍለዋል፡፡ ተጠሪ በአሁኑ ደረጃ ያቀረበችው ክስ የሚስተናገድበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከመረመረ በኂላ፣ ብዙዎች በክሱ የተመለከቱት ክፍያዎች ውድቅ ያደረገ ሲሆን፣ ከዓመት ዕረፍት ፈቃድ ጋር ተያይዞ ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ ግን በመቀጠል አመልካች እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ ያቀረበው፣ተጠሪ ለባለቤቱ ሊከፈል ይገባው የነበር ነው በማለት ያቀረበችው የክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ነው ወይ? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው የተጠሪ ባለቤት የነበረው መሐመድ ሁሴን ከአመልካች ጋር አድርጎት የነበረው የስራ ውል መቋረጥን መነሻ በማድረግ በአመልካች ላይ ክስ መስርቶ ሲከራከር ከቆየ በኂላ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ሞቶአል፡፡ ከዚህ የተነሣም ተጠሪ ክርክሩን ስትከታተል ቆይታለች፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር በመመርመር አመልካች የማስጠንቀቂያ እና የስራ ስንብት ክፍያዎች እንዲሁም ወጪና ኪሣራ ይከፈል ሲል ወስኖአል፡፡ ተጠሪ በስምዋ አዲስ ክስ የመሠረተችው ከዚህ በኂላ ነው፡፡ አመልካች የክሱን መቅረብ የተቃወመውም እነዚህን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ነው ፡፡

ከፍ ሲል እንደገለጽነው ተጠሪ በክስዋ ላይ ያመለከተችው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲሰጡአት ሲሆን፣ ከዚህም አንዱ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሚመለከት ነው፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የተቀበለውም በዚህ ረገድ የተጠየቀውን ክፍያ ብቻ ሲሆን፣ ለመቀበሉ የሰጠው ምክንያትም አመልካች በማመንም ይሁን በመካድ መልስ አልሰጠበትም የሚል እንደሆነ ከውሳኔው ተመልክተናል፡፡ በበኩላችን እንደምናየው አመልካች የክሱን መቅረብ በአጠቃላይ ተቃውሞ ተከራክሮአል፡፡ ለዚህ የሰጠው ምክንያትም የተጠሪ ባለቤት መስርቶት በነበረው ክስ ተጠቃሎ የተጠየቀ ወይም አንድ ላይ ሊጠየቅ ይገባው

የነበረ ነው የሚል ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ መልክ የቀረበውን የአመልካች ክርክር በመገንዘቡ በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ ይህ መሰል መቃወሚያ ሲቀርብም አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ማንኛውም የፍትሐብሔር ክስ ሲቀርብ ስለ ክሱ አቀራረብ በተመለከተ የተቀመጡትን የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ድንጋጌዎች ሊከተል እንደሚገባ የሚያከራክር አይደለም፡፡ የተጠሪ ባለቤት አቅርቦት የነበረው ክስ ከአመልካች ላይ የሚፈለገውን መብት የሚዘረዝር እና ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ እንደነበር ይገመታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክሱ የተወሰኑትን ክፍያዎች ሳያካትት ቀርቶ ነበር አልተባለም እንጂ ቢባልም ኖሮ ከፍ/ቤት የተገኘ ፈቃድ ሳይኖር በሌላ አዲስ ክስ ሊጠየቅ እንደማይችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.216 (4) ተመልክቷል፡፡ይህ ጉዳይ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 5 አንፃር ሲታይም በአዲሱ ክስ (ተጠሪ ባቀረበችው) እና ቀደም ሲል ክርክር ተደርጎበት የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘው ክስ መካከል ልዩነት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረባቸው ክስ በድጋሚ የሚታይበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔም ከዚህ አኳያ ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07717 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 64777 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348 (1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ የጠየቀችው የዓመት እረፍት ፈቃድ ክፍያ እንደ ሌሎች ክፍያዎች ተቀባይነት የለውም፡፡ ሊከፈላት አይገባም ብለናል፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት